# አውደ ኢትዮጵያ

ሰኔ 2000 | የኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሲን ህጋዊ መንግሥትንና ፍትሃዊ ስርዓትን የመጠየቅ መብት አለው! | ልዩ እትም 2

## አንድነት ለዲሞክራሲ ለፍትህ ፓርቲ መሥራች ጉባዔውን አካሄደ፤ አመራሩንም መረጠ

አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ባለፈው ረቡዕ ሰኔ 11 ቀን የመስራች ጉባዔውን በተሳካ ሁኔታ ማካሄዱንና የአመራር አባላቱንም በዲሞክራሲያዊ መንገድ መምረጡን ዘጋቢዎቻችን ከአዲስ አበባ ገለጹ። ጉባዔው ሊካሄድ ታቅዶ የነበረው፤ ቅዳሜ ሰኔ 7 ቀን በኢምፔሪያል ሆቴል ሲሆን፤ ገዥው ፓርቲ በፈጠረው ማሰናከያ ምክንያት መስተጓጎሉ፤ የሚዘነጋ አይደለም።

ረቡዕ እለት፤ ጉባዔው የተካሄደው በፓርቲው ጽ/ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ በተተከለ ድንኳን ውስጥ ነው። የጉባዔው ተሳታፊዎች ከሀገሪቱ አራቱም ማዕዘናት የተውጣጡ፤ ከየክልሎቻቸው የተወከሉ 400 የሚሆኑ የጠቅላላ ጉባኤው አባላቶች ናቸው። ጉባዔውን በእንኳን ደህና መጣቹህ ንግግር የከፈቱት፤ የአዘጋጅ ኮሚቴ ሊ/መንበር የሆኑት ኢንጅነር ግዛቸው ሽፈራው ናቸው።

በመቀጠልም፤ ከስድስት ሰዓታት በላይ የፈጀ ውይይትና ክርክር በማድረግ፤ የፓርቲውን ፕሮግራምና የመተዳደርያ ደንብ በሙሉ ድምጽ አጽድቋል። በዚህ ጊዜም፤ በደጋፊ ወጣቶች ተቀነባብሮ ለጉባዔተኞቹ የቀረበ መዝሙርና የፓርቲው ዓርማም ተቀባይነት አግኝተው ጸድቀዋል።

ጉባዔው፤ ከቀትር በኋላ ፕሮግራሙ፤ እንደገና ስድስት ሰዓታትን በመውሰድ፤ የአመራር አባላቱን መርጧል። በዚህም መሰረት፤ ለብሔራዊ ምክር ቤት አባላት 105 ዕጩዎች ተጠቁመው፤ 60 በሙሉ አባልነትና 15 በተለዋጭ ዓባላትነት ተመርጠዋል። 60ዎቹ ተመራጭ የብሔራዊ ምክር ቤት አባላት፤ በበኩላቸው ተሰብስበው ከመሃከላቸው 18 የሥራ እሰፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን መርጠዋል። ከነሱ ውስጥም ስድስቱ የፓርቲው ከፍተኛ አመራር በመሆን ተመርጠዋል። የምርጫው ውጤት ሲገለፅም፤ ወ/ት ብርትኳን ሚዴቅሳ ሊቀመንበር፤ ኢንጅነር ግዛቸው ሽፈራው ም/ሊቀመንበርና የድርጅት ጉዳይ ሃላፊ፤ ዶ/ር ያቆብ ሃ/ማርያም ም/ሊቀመንበርና የውጭ ጉዳዮች ሃላፊ፤ ዶ/ር ሀይሉ ዓርዓያ ምክትል ሊቀመንበርና የህዝብ ግኑኝነት ሃላፊ፤ አቶ ተመስገን ዘውዴ (የፓርላማ ዓባል የሆኑ) ምክትል ሊ/መንበርና የእስተዳደርና ፋይናንስ ጉዳይ ሃላፊ፤ አቶ አስራት ጣሴ ዋና ጸሓፊ በመሆን ተመርጠዋል። ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም፤ የ<u>አውደ</u> ዝግጅት ክፍል ለጉባአተኞቹ በአጠቃላይ፤ እንዲሁም ለተመራጬች፤ ለተሳካ ሥራቹህ እንኳን ደስ ያላቹህ ለማለት ይወዳል። የወዲፊት ሥራቹህም እንዲሁ የተሳካ እንዲሆን መልካም ምኞቱን ይገልፃል። ከዚህ ጋር በተያያዘም፤ <u>አውደ</u>፤ ተመራጭ ሊ/



አቶ ተመስገን ዘዉዴ ፤ ሊ/መንበሯን ወ/ት ብርቱካንን ፤ ምክትል ሊቀመናብርት ኢንጂነር ግዛቸዉ ሽፈራዉ፤ ፤አቶ አስራት ጣሴ ፤ ዶ/ር ኃይሉ ዓርዓያ ፤ ዶ/ር ያዕቅብ ኃይለማሪያም





መንበሯን፤ ወ/ት ብርቱካንን አነጋግሯል። በውስጥ ገጻችን ያንብቡት።

የጉባዔውን ሂደት በንቃት ሲከታተሉ የነበሩ ተንታኞች እንዳብራሩት ከሆነ፤ ምርጫው ፍፁም ዲሞክራሲያዊ ነበር። ተመራጩቹም፤ ከተለያየ ብሔረሰብ፤ ፆታ፤ ሓይማኖት፤ ዕድሜና የትምህርት ደረጃ የተወጣጡ መሆናቸው፤ የኢትዮጵያን ገጽታ የሚያንፀባርቅ ነው ብለዋል። አንድ ዋና የፖለቲካ ፓርቲ በኢትዮጰያ ዉስጥ በሴት ሲመራ ይህ የመጀመሪያ በመሆኑ በዚህ መሰራች ጉባኤ ታሪክ ተሰርቷል። ከዚህም በላይ ከተመረጡት አሥራ ስምንት የሥራ አስፈጻሚ አባላት ዉስጥ 17 በመቶዎቹ ሴቶች ናቸዉ። ከነዚህም ውስጥ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ፣ የትግራይ ተወላጇ ወ/ሮ ሸዋዬ ኪሮስ እንዲሁም ትዉልዳቸዉ ሃረር አካባቢ የሆኑት ወ/ር ላቀች ይገኙበታል። የፓርቲው ከፍተኛ አመራር አባላትም እንደዚሁ የብሄረሰብ ስብጥር ያላቸው ናቸው። ሊቀመንበሯ ወ/ት ብርቲካ ሚደቅሳ አዲስ አበባ ፈረንሳይ ለጋሲዮን አካባቢ የተወለዱ ሲሆን፣ ምክትል ሊቀመናብርት ኢንጂነር ግዛቸዉ ሽፈራዉ በጅሩ፣ ዶ/ር ያዕቅብ ኃይለማሪያም በእምድበር(ጉራጌ)፣ ዶ/ር ኃይሉ ዓርዓያ በማይጨው (ትግራይ)፣ አቶ ተመስገን ዘዉዴ በሳዉላ ቡልቂ (ገሙጎፋ)፣ እንዲሁም አቶ አስራት ጣሴ ሸዋ ክፍለ አገር ዉስጥ የተወለዱ ናቸዉ።

ከምርጫው በኋላ ወ/ት ብርትኳን ባደረጉት ንግግር፤ ካሳለፍነው ውጣ ውረድ በመማር በፓርቲያችን ግልፅነትና ተጠያቂነት፤ በፖለቲካ አካሄዱ ላይ ተወያይተንና ተከራክረን በአመራሩ መሃከል መግባባት ላይ በመድረስ፤ አሰራራችንን አጠናክረን እንቀጥላለን ብለዋል።

የአንድነት ፓርቲ ብሄራዊ ምክር ቤት አባል ሆነው የተመረጡት ፐ/ር መስፍን ወ/ማርያም፤ በሰጡት አስተያየት፤ ፓርቲያችን ጠንካራ ሁኖ ለመቀጠል ከአሁን በኋላ የሚያግደው ነገር የለም ብለዋል። ስለ ወ/ት ብርትኳን ሊቀመንበር ሆኖ መመረጥም አስተያየታቸውን ሲሰጡም፤ "በጣም ጠንካራ ወጣት ሴት ናት፤ በዘር በቋንቋ፤ በሃይማኖት ሳንከፋፈል፤ እዚህ ለመድረስ የበቃነው በሷ አሰባሳቢነት ነው። ስለብቃቷ አትጠራጠሩ፤ ከኛ የሚጠበቀው እሷን ማገዝ ነው" ብለዋል።

የፓርቲዉ መስራች ጉባዔ ከተጠናቀቀ በኋላ የሚያስፈልጉ ሰነዶች በሙሉ ተሟልተዉ ለምርጫ ቦርድ እንደገቡ የአመራር አባላቱ ገልጸዉ ፤ ከምርጫ ቦርድ አስፈላጊዉን ትብብር እንደሚያገኙና ቦርዱም በአጭር ጊዜ ውስጥ ሕጋዊ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸዉ ያላቸዉን ተስፋ ገልጸዋል። የምርጫ ቦርድ ሕጋዊ ፈቅድን እስኪሰጥ ድረስ ፓርቲዉ በሕገ መንቀሳቀስ እንደሚችልና ሰላማዊዉ የፖለቲካዊ ሥራ ከመቼውም በበለጠ እንደሚቀታጠል ተገልጿል። የምርጫ ቦርዱ፤ ስለ ፓርቲ ህጋዊ ምስረታ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ መልስ መስጠት የሚጠበቅበት ሲሆን፤ በዚህ ጊዜ መልስ ካልተሰጠ፤ በአዋጁ መሰረት፤ ፓርቲው ህጋዊ ፈቃድ እንዳገኘ ይቆጠራል። ይሁን እንጂ፤ አዲስ የወጣው የፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ፤ የምዝገባውን ሂደት ሊያስተጓጉል ይችላል ሲሉ፤ ተዛቢዎች ስጋታቸውን ይገልጻሉ።

# የአንድነት ፓርቲ ምስረታ፤ ለህዝብ ተስፋ ለኢሕአዴግ ግን ፍርሃት

## የአውደ-ኢትዮጵያ ርዕሰ-አንቀፅ

ገዥው ፓርቲ ኢሕአደግ ከምርጫ 97 በኋላ የሚከተለው ስትራቴጂ የማዋከብና የማገድ ባህሪ እያደረ አስደንጋጭ ደረጃ ላይ ደርሷል። ሰሞኑን በፓርላማ እንዲጸድቁ የሚጠይቁ ሕጎች ዜጎች በሀገራቸው በነጻነት መንፈስ የሚሰሩበት፣ የሚናገሩበትና የሚደራጁበትን መብት ሙሉ ለሙሉ የጣሰ በየትኛውም «ዲሞክራት ነኝ» በሚል መንግስትም ሆነ ድርጅት የማይታሰቡ ናቸው። ከራሱ ሕገ-መንግስት ጋር የሚጣረሱ ጭምር።

ኢሕአዴግ ላለፉት 17 ዓመት ሃገሪቱን ሲገዛ በሌኒኒስት አካሄድ ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ ለአገዛዝ አመቺ አሰራር በመዘርጋት በሀገሪቱ ማህበራዊ ሕይወት ንግድ እና ኢኮኖሚ ፍላጎት ውስጥ ረዥም እጁን ሰዷል። ይህም ሥልጣኑን ለማስረከብም ሆነ ለማጋራት ምንም አይነት ምልክት የማያሳይ የአህዳዊ አገዛዝ ስትራቴጂዉን የሚይሳይ ነው። ይህን ስትራቴጂ በሚገባ ለመጠቀምም ሌሎች የፖለቲካም ይሁን የሲቪክ ማህበራትን በመዋጥ በማጥፋት ላይ ይገኛል።

ኢሕአዴግ በቃል የመድበል ፓርቲ ስርዓት የዘረጋ እያስመሰለ ቢናገርም በተግባር ግን አሃዳዊነቱን ደጋግሞ አሳይቷል። የሰሞኑ የፕሬስ ሕግ፤ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና የፖለቲካ ፓርቲዎችን አደረጃጀትን የሚወስኑ ሕጎች፤ በተለይ የሚጠቀሱ ናቸው።

ነጻዉን ፕሬስ ለማፈን ላለፉት 16 ዓመታት ሳይታክት ሲሰራ የነበረ ፓርቲ ተመልሶ ሌላ አማራጭ የሚያሳጣ ፍጹም ነጻ ሊባል የማይችል፣ የመናገርና የመጻፍ ነጻነትን የሚገድብ ሕግ ለማዉጣት በዝግጅት ላይ ይገኛል። ረቂቅ የፕሬሱ ሕግ ከዛሬ ስድስት አመታት በፊት ጀምሮ ሲያከራክር የነበረ ከተለያዩ አለም አቀፍ ተቋምትና ዲፕሎማቶች ትችት ሲሰነዘረበት የከረመ ሕግ መሆኑና አሁን ሊጸድቅ ከጫፍ መድረሱ የኢሕአዴግን አምባገነናዊ አካሄድ አጉልቶ የሚያሳይ ተግባር ነው። ከዛሬ ስድስት ዓመታት በፊት ኢሕአዴግ በሀገሪቱ ተቀባይነት ያለው በየትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፣ በየትኛውም የፕሬስ ፕሮፖጋንዳ የማይረታ ቡድን አድርጎ ራሱን ያይ ስለነበረ ምርጫ 97 የሚመጣበትን ተጽእኖ እስኪያይ ድረስ ረቂቁ ሕጉን አስቀምጦ ቆይቷል። የምዕራባዉያንን የገንዘብ ትሩፋትን ላለማጣት ሲልም ሕጉን ያለዝባል ተብሎ ሲጠበቅ ነበር።

ምርጫ 97 መጥቶ ድርጅቱ ራሱን የት ቦታ እንዳለ ለማየት ሲገደድ፣ በሕዝብ ተቀባይነት እንደሌለው ሲረዳ ሕጉን ለማዉጣት የነጻ ፕሬስንና የዲሞክራሲ ግንባታን ለማፈን ተነሳ። የአውሮፓ መንግሥታትንም ገንዘባችሁን ኋላ ኪሳችሁ ከታችሁ ሂዱ፤ ከሥልጣኔ የሚገፉኝ አንዳች የለም ሲል ሕጉን ለማጽደቅ ደረሰ።

በሃገር ቤት የዚህ ሕግ መዉጣት ራስ ምታት የሆነባቸው፤ የዲሞክራሲ ጉዙአችን ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ እየሄደ መሆኑ ያሰጋቸው፣ የፕሬሱ የዲፕሎማትና የሲቪክ ማህበራቱ የየራሳቸው ሃሳብ በመግለጽ ሕጉ እንዲለዝብ እየጮኹ ባለበት ጊዜ ነው መንግስት ሌሎች ተጨማሪ አፋኝ ሕጎችን እያረቀቀ ለፓርላማ የሚያቀርበው። ከነዚህም ውስጥ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የፖለቲካ ፓርቲ ማቋቋሚያ የሚደነግገው ሕግ እንዲሁም የብሄራዊ ባንክ ማሻሻያ አዋጅ የሚጠቀሱ ናቸው።

ጠ/ሚ መለስ ለእነዚህ ሕጎች መዉጣት እንደ ምክንያት ያቀረቡት እንደሌላው ጊዜ የማይዋጥ አመክንዮን አይደለም። ድርጅታቸው ፍርሃት ይዞት መሆኑን እንጂ። አቶ መለስ እንዲህ በግልጽ ሲናገሩ ምናልባት የመጀመሪያ ሳይሆን አይቀርም። ድርጅታቸው ፍርሃት ውስጥ ነው። እንደ ዘመነኛው ፖለቲካ ከሁኔታዎች ጋር መተጣጠፍ ያቃተው እንደ እርሳቸው አባባል «ተገትሮ ለመሰበር የደረሰ» ሆኗል። « ገደል ጫፍ ላይ ቆሞ ብሎ ሂድ ቢባል ወደትም መሄድ አይችልም» ነበር ያሉት ጠ/ሚኒስትሩ። ድርጅታቸው ዉጤታማ መሆን ይፈልጋል። ከዚህ በፊት ምርጫ 97ን ያሞቁትና የሕዝብን ተሳትፎ ያሳደጉት የግሉ ፕሬስና የሲቪክ ማህበራት መሆናቸው ኢሕአዴግ በሚገባ አረጋግጧል። እነዚህ ማህበራት ለአንድ አገር የዲሞክራሲ ግንባታ እድገትና ልማት ከፍተኛውን ሚና እንደሚጫወቱ ግልጽ ነው፤ በተለይም እንደኛ ባለ ደሃ አገር።

ነጻው ፕሬስ የመንግስትን አካሄድ ይተቻል፣ ሲቪክ ማህበራት በተቀረጹበት ዓላማ እየተመሩ ገንዘባቸዉን እያፈሰሱ ሕዝቡ በሀገሩ ለሃገሩ የመኖር የመስራት የመጠየቅ የሥልጣን ባለቤት .... የመሆኑን ምሥጢር ይነግሩታል ያነቁታል። ይህ ነው እንግዲህ አቶ መለስን ፍርሃት ዉስጥ የጣላቸው። የ97 መርጫ ወንበራቸዉን ያነቃነቀው ቅንጅት የተባለ ማዕበልም በነዚህ ማህበራትና የሜዲያ አባላት እገዛ አግኝቶ እንደነበረ አቶ መለስ ይናገራሉ። ለድርጅታቸው ዉጤት ማጣትም ይኸው የነርሱ ጣጣ ሆኖ ከቅንጅት መሪዎች ጋር ተደምረው ከሁለት አመት በላይ ወህኒ ለመሰንበት ተገደዋል።

አቶ መለስ የፈሩለትን ሥልጣን ለመጠበቅ ድርጅታቸው ከጊዜ ከሁኔታዎችና ከሕዝብ ፍላጎት ጋራ አጣጥሞ ከመሄድ ይልቅ አፋኝ ሕጎችን ማዉጣት መርጠዋል። ድርጅታቸው በስልጣን ላይ ተገትሮ እንዲቀር ወጤት እንዲያጣ ከገደል ጫፍ እንዲቀመጥ ያደረገው የራሱ አይዲዮሎጂ እንጂ ማህበራቱ አለመሆናቸዉን ለመረዳት የፓርቲዉን የውስጥ አሰራሩ አይመረመርም። የሌሎችን ተመክሮ አያይም። ይልቅ ችግሮችን ዉጫዊ ያደርጋል። ራሱ ያለፈበትን መንገድ ዞሮ ከማየት ሌሎች የሄዱበትን መንገድ መኮነን ይቀናዋል። የሰሞኑ ረቂቅ ሕጎችም የሚያሳዩት ይህንኑ ነው።

በሕዝብ በጎ ፍቃድ፣ በባለሃብት ገንዘብ የሚያቋቁመው ድርጅቶች በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ጠበል ካልተጠመቁ መንገዳቸው ዝግ፣ ጽድቃቸው የመርገም ጨርቅ ነው።

ሌላው ኢሕአዴግ በፍርሃት ያራደው ሌላ የሰሞኑ ወሬ የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ መመስረት ነው። ፓርቲው ከዛሬ ሶስት አመት በፊት ቅንጅት ያነሳቸዉን መርህዎች ተከትሎ፣ የከፈላቸዉን ዋጋዎች ከጫፍ አደርሳለሁ ብሎ የተነሳ ፓርቲ ነው። አሁን በአገራችን ባለው ጠባብ የፖለቲካ ሜዳ በብቸኝነት ሕጋዊና ሰላማዊ ትግል ለማድረግ የተዘጋጀው «አንድነት» ከቅንጅትም በላይ ኃላፊነት አለበት። የፖለቲካው ሜዳው እንዲህ በታፈነበት ሁኔታ ትግሉን ለማካሄድ መነሳት አስቸጋሪ መሰናክሎችን ማለፍን፣ ቁርጠኝነትን ይጠይቃል። ይህ ቁርጠኝነትና እልህ በመሪዎቹ መታየቱ ለሕዝብ ተስፋ ለኢሕአዴግ ፍርሃት ሆኗል። ኢሕአዴግ የቅንጅትን መሰንጠቅ ተከትሎ ትንሽ የእፎይታ ጊዜ አግኝቶ የነበረ ቢሆንም እነዚህ በሕዝብ ከበሬታ ያገኙ ታጋዮች ተመልሰው ወደ ትግል ሜዳ መምጣታቸው ጭልጥ ያለ ፍርሃት ውስጥ እንዲገባ አስገድዶታል።

ኢሕአዴግ ይህንን ፍርሃቱን በዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር ከመጋፈጥ ይልቅ «የአንድነትን» ፓርቲ መንገድ መዝጋትን አማራጭ አድርጎ ይንቀሳቀሳል። የአንድነት አመራሮችንም በተለያዩ ዘዴ የርሱ ፍርሃት እንዲጋባባቸው ተጽእኖ ይፈጥራል። አልሆን ሲለው ደግሞ የምሥረታ ሂደታቸዉን ለማከናወን የሚያስችላቸዉን ተግባራት እንዳይፈጽሙ፣ አባላትን እንዳያሰባሰቡ፣ ከምርጫ እንዲከለከሉ፣ ስበሰባ እንዳያካሂዱ በማድረግ ይፈትናቸዋል።

የቅንጅት ስሙ እንጂ አላማው የማይሞትና የማይለወጥ መሆኑን ያልተረዱ የወያኔ አድሃሪዎችም፣ ፍርሃቱን ተጋርተው የሕዝብን ሞራልና ተስፋ ለመጠገን በጉጉት የሚጠበቀዉን ፓርቲ ለማኮላሸት ከላይ እታች ይባዝናሉ። ከነዚህም ውስጥ በዋነኝነት የምርጫ ቦርድን የሃላፊነት ካባ የተሸለሙት አካላት ይጠቀሳሉ። አንድነትን ለመመስረት በሃገሪቱ ሕግ መሰረት የድጋፍ ማሰባሰቢያ ፎርም እንዲሰጣቸው ሲጠይቁ ሲጅመር በቀጠሮ፣ ቀጥሎም በክልከላ እንዳሰናበታቸው የሚያታወስ ነው። ቦርዱ በተደጋጋሚ ቢጠየቅም ምልሽ ባለመስጠቱ የፊርማ ማሰባሰቡ ሥራ ያለድጋፍ ደብዳቤ እንዲደረግ አስገድዷል። ቀድሞዉንም «አንድነት» የተነሳለትን የሰላማዊና ሕጋዊ ትግል ዓላማ ላለመሳት ቦርዱን ጠየቀ እንጂ የድጋፍ ደብዳቤ የሚያመጣው ለውጥ አልነበረም። የምርጫ ቦርድን የእስካሁኑ ጉዞ ምን እንደሆነ የሚያወቅ በመሆኑ ምንም የምንጠብቅበት ነገር ባይኖርም፣ የወያኔን ፍርሃት ያስታግስ መስሎት የሚሰራው አስቂኝ ተግባር ግን እያስተዛዘበን አለን።

ሌላው የመንግስት ቀኝ እጅ፤ ፖሊስ፤ «አንድነት» ፓርቲ ለማወክ ቀዳሚ ሆኖ ተገኝቷል።«አንድነት» የጠራዉን ጠቅላላ ጉባዔ በማገድም የአቶ መለስን ፍርሃት ያቃልል መስሎ ለመታየት ሞክሯል። «አንድነት» ለዲሞክራሲና ለፍትህ ቅዳሜ ሰኔ 11 ቀን በኢምፔሪያል ሆቴል ጠቅላላ ጉባዔዉን ለማድረግ፣ ሕገ ደንቡን ለማጽደቅና የአመራር አባላዩን ለመምረጥ ፕሮግራም ይዞ የነበረ ቢሆንም ምንም አይነት በሕግ የተሰጠ ስልጣን የሌላው የአዲስ አበባ ፖሊስ ጉባዔው እንዳይደረግ ከልክሏል። በጣም የሚገርመው ደግሞ በፓርቲው ጽ/ቤት ግቢ ዉስጥ ስብሰባዉን ማካሄድ እንደማይችሉ ሲነግሯቸው መስማት ነው። ፖሊሶቹ ከላይ ተሰጠ ባሉት ትዕዛዝና እግዳ ምክንያት «አንድነት» ጠቅላላ ጉባዔዉንና የአመራር አባላቱን ምርጫ እንዲያራዝም አስገድዶታል። የአቶ መለስና አጋሮቻቸዉን ፍርሃት ግን የሚቀጥል እንጂ የሚቆም አይመስልም። «የአንድነት» ጊዚያዊ አስተባባሪዎችም እገዳዉን እንደ መጀመሪያው የፓርቲው ድል በማየት ተበረታቱ እንጂ አልተሻማቀቁም።

የጠቅላላ ጉባዔው ዝግጅት አስተባባሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ እንጂነር ግዛቸው ሽፈራው በወቅቱ የተሰማቸዉን ስሜት ለማወቅ ቃላት ከአንደበታቸው መጠበቅ አያስፈልግም ነበር። ሐዋርያው ጳውሎስ በክርስቶስ ስም ታስሮና ተገርፎ ሲወጣ ይነበብበት ነበር የሚባለው ጸአዳ ፊታቸው ላይ ባይታይም፣ ግርምታቸው፣ የአባሎቻቸዉና የደጋፊዎቻቸው ጽናት፣የወያኔ ፍርሃት እንዳይከፋ እንድዳረጋቸው ማወቅ ግን አያዳግትም፡ እርሳቸዉም ቢሆኑ እግዳው የፓርቲያቸው የመጀመሪያ ድል የኢሕአዴግ ፍርሃት ሆኗል ነበር ያሉ እንጂ አልተቀጩም።

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በበኩላቸው እንደ ሕግ ባለሙያነታቸው አንቀጽ እየጠቀሱ ክልከላው ሕጋዊ መሰረት እንደሌለው ለሚጠይቃቸው ጋዜጠኛ ሁሉ ሲናገሩ በተከፋ ፊት ሳይሆን « ኢሕአዴግ እንግዲህ ተራው ያንተ ነው፤ ፈሪ አይጸድቅም » የሚሉ ነበር የሚመስለው።«አንድነት» ለዲሞክራሲና ለፍትህ የኢሕአዴግን ትልቁ ራስ ምታት፣ ትልቁ ፍርሃት መሆኑን አመራሮቹ የበለጠ ይረዱታል። የሕዝቡ ሞራል በአንባገነን አመራሮች፣ አፋኝ ሕጎችና በኑሮ ዉድነት በደቀቀበት፣ ፓለቲካኖች የአፍ ዲሞክራሲ አስተምህሮች ስም እየጠሩ የዜጎችን የለውጥ ፍላጎት በሚያኮላሽበትጊዜ «የአንድነት» መመስረት ብዙ እንድንጠብቅ ያደርገናል። በሕዝብ ስም የሚነግዱ የአፍ ፖለቲከኞች የጎዱትን፣ የኢሕአዴግ እንቅፋት እያንኮታኮተ እዉን የዲሞክራሲ ግንባታ «አንደንት» እንዲምልስልን እንሻለን። የኢሕአዴግ ፍርሃት፣ ግትርነትና ውጤት ማጣት፣ የራሳቸዉም ያለፈ ተመክሮ ትምህርት ሆኖዋቸው የሕዝቡን ተስፋ በእርግጥ እንዲመልሱት እንጠብቃለን።

# «ቅንጅት በአንደበት ካገለገሉት ጋር በዓላማ ጽናት ተለያይተናል» _ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ

<u>አውደ</u> - እንኳን ደስ አልዎት

<u>ብርትኳን</u>- እንኳን አብሮን ደስ አለን።

<u>አውደ</u>፦ ከምርጫዉ እንጀምር ግልጽና ዲሞክራሲያዊ ነበር ?



የአሁኑ ምርጫ ከዚህ በፊት በቅንጅት እያለን ካደረግነው፣ ችግሮችን አይቶ ከማረምና ትክክለኛ አሰራር ከመገንባት አኳያ እመርታ አሳይተንበታል ብዬ አምናለሁ። በኔ በኩል ከምርጫዉ በፊትም ሆነ ከምርጫዉ በኋላ በተለይም በምርጫዉ እለት ግልጽነትና ዲሞክራሲያዊነት በተከተለ አካሄድ የተከናወነ ነዉ።ከመነሻዉ ገለልተኛ የሆኑ የምርጫ አስፈጻሚ አካላት ከጠቅላላ ጉባዔዉ ተመርጠዉ ጠቅላላ የምርጫ ሂደቱን ተረክበዉ በገለልተኝነት ያስፈጸሙበት ሂደት ነበር።ምርጫ አስፈጻሚዎቹ አስተባባሪ ኮሚቴዉ ያቀረባቸዉን እጩዎች ተቀብሎ ሌሎች 15 አባላት ጨምሮ አስመርጧል። በስብጥሩ ሲታይም ከየክልሉ የተወከሉና ሴቶችንም ያካተተ ነበር። በአጠቃላይ ምርጫዉ በጣም ነጻና በጣም ገለልተኛ ዉጤቱም ያማረ ነበር።

<u>አውደ</u>- በቅደመ ምርጫ ወቅት አሉታዊ የምረጡኝ ቅስቀሳ ነበር ስለሚባለዉስ ?

<u>ብርትኳን</u>፦በሀገር ደረጃ የዲሞክራሲ አካሄዳችን ችግር ያለበት ነዉ። ማህበረሰባችን በተለይ በምርጫ ለይተን ብናየዉ ብዙ ችግር ያለበት ነዉ። ከነዚህ ችግሮች መሀከል ዉድድሮችንና ፉክክሮችን ግልጽ አለማዉጣትና አሉታዊ ቅስቀሳዎችን ማድረግ ሊጠቀሱ ይችላሉ። ከዚህ አኳያ ከምርጫዉ በፊት የተወሰነ ችግሮች አጋጥመዉን ነበር ማለት ይቻላል። በአጠቃላይ ሲታይ ግን ዲሞክራሲያዊ መንገድን ጠብቆ በግልጽ ለድርጅቱ ማን ይጠቅማል በሚል ይደረጉ የነበሩ ዉይይቶችና የሎቢ ስራዎች ይበልጡ ነበር።

<u>አውደ</u> - አዲሱ ፓርቲ አንድነት፤ ከሌሎች የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች፤ በአደረጃጀትና በአቀራረብ እንዴት ይገለጻል?

<u>ብርትኳን</u>፦በአጭሩ ለማስቀመጥ አዲሱ ፓርቲ አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ፣ የቅንጅት አላማና መንፈስ ወራሽ ነዉ። ከቀድሞ ቅንጅት የምንለየዉ በምርጫ በተሳተፍንባቸዉ፣ ከምርጫ በኋላ ፓርቲዉ ላይ በደረሰዉ ጥቃት፣ ከታሰርንባቸዉ፣ ከእሥርም በኋላ በመሃከላችን ከተፈጠሩ ችግሮች ትልቅ ትምህረት አግኝተን የያዝነዉን አላማ እዉን ለማድረግ የሚችል ፓርቲ ማቋቋማችን ነዉ። አንድ ፓርቲ ሊያሟላ የሚገባዉን ነገሮች መሟላቱን ፣ የጎደለን ምን እንደሆነ አዉቀንና ከ 97 እስከአሁን ባለዉ ሂደት ትምህርት የወሰድንበት እንዲሁም አንድነት ፓርቲ የቅንጅትን አላማና መንፈስ አንግቦ በከፍተኛ ድርጅታዊ ጥንካሬ የመጣ ፓርቲ በመሆኑ ለየት ያደርገናል።

ቅንጅት ሕዝቡ ለዲሞክራሲና ለብልጽግና የነበረዉን ተስፋና ፍላጎት መልክ አስይዞ የመጣ ድርጅት ነበር። ያኔ ግን መሬት ለማስረገጥ የሚችል ድርጅታዊ ጥንካሬና ብቃት ገንብቶ ነበር ወይ ? ብለን ብንጠይቅ ምላሹ አሉታዊ ሆኖ እናገኘዋለን። ይህ ድርጅታዊ ጥንካሬ ማጣት ቅንጅትን ከዉጫዊ ጥቃት ባልተናነሰ ሁኔታ የዉስጥ ችግሩ አድክሞታል። ሕዝቡም በፓርቲዉ ላይ ያለዉን እምነት በተወሰነ መልኩ ሸርሽሯል።

ስለዚህ አንድነት ከተቋቋመ በኋላ የሚቀጥለዉ እንቅስቃሴ በአብዛኛዉ ድርጅቱን ከላይ እስከታች በማጠናከር፣ አባላቶችን በግለሰባዊ ግንኙነት፣ ታማኝነትና በሌሎች በመሳሰሉት ግንኙነቶች ሳይሆን በመሃከላችን ያለዉ ትስስር በፖለቲካ ግንዛቤ ላይ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል። ስለዚህ ሕጋዊነትን ከማግኘት ቀጥሎ ዋና ትኩረታችን የሚሆነዉ መዋቅሩን መዘርጋት፣ በፖለቲካ እምነቶች ላይ የተመሰረተ ጠንካራ ትስስር መፍጠርና የፓርቲዉን የዉስጥ አሰራር ፍጹም ግልጽነትን ዲሞክራሲያዊነትን የተከተለ እንዲሆን ማድረጉ ላይ ነዉ። ፓርቲያችን ክፍት ዲሞክራሲያዊና ችግር በሚገጠመዉ ጊዜ የማይገፋና የማይወድቅ ዘመናዊና ጠንካራ መሆኑን እስክናረጋግጥ የማደራጀት ስራ እንሰራለን። ሌላዉ ልዩነታችንም ከዚህ ላይ ነዉ።

<u>አውደ</u>፦በዚህ አቀራረባችሁ በ 97 የነበረዉን የሕዝብ ተሳትፎና የፖለቲካ መነቃቃትን መመለስ ይቻለናል ብላችሁ ታምናላችሁ?

<u>ብርትኳን</u>፦የማይቻልበት ምንም ምክንያት አይታየኝም። በርግጥ የሀገሪቷ የፖለቲካ ድባብ ከ97 በተባባሰ፣ ለተቃዉሞ ያለዉ ስፍራ በጣም የተጣበበ ለመድብለ ፓርቲ ሥርዓት ግንባታና ለዲሞክራታይዘሽን አስፈላጊ የሆኑ ተቋማት የተዳከሙበት፣ ፕሬሱ በከፍተኛ መሸማቀቅ የሚሰራበት ፣ ለዜጎች የዲሞራሲና ሰብዓዊ መብት በጣም ተብበሰዉ የቀጠለበት ሁኔታ ነዉ ያለዉ። ቢሆንም የሕቡን የሥልጣን ባለቤትነት የሚረጋገጥበት አላማን ማዕከል አድርጎ የሚደረግ ሰላማዊ ትግል በገዢዉ ፓርቲ በጎ ፍቃድና በገዢዉ ፓርቲ ተባባሪነት ላይ የሚመሰረት አይደለም። ገዢዉ ፓርቲ የራሱ ኃይል እንዳለዉ ሁሉ ማህበረሰቡም የራሱ ኃይላ አለዉ። በተለይ በሰላማዊ ትግል የሚገለጠዉ ኃይል ከዚህ ችግር ማለፍ ይቻላል ብሎ ማወቁ ነዉ። ሕዝቡ ከተጋረጠበት የሚበልጥ ኃይል በሰላማዊና በዲሞራሲያዊ ትግል የሚገለጥ አራማጅ ኃይል እንዳለ ማመን አለበት።

ገዢዉ ያለዉን አፈናና ትግዳሮት እያጠናከረ ሲመጣ በአንጻሩ ሰላማዊዉን ትግል የሚያደርገዉ አካል ተስፋዉ እየጨመረ፣ በራሱ ላይ ያለዉን እምነት እያጠናከረ፣ ማህበረሰባዊ መሰረቱን እያሰፋፋ በጽናት በመቆም በሰላማዊ ትግል ማዕቀፍ ዉስጥ ያሉ የተለያዩ ታክቲኮችን በመጠቀም ገዢዉ ሳይወድ በግዱ ለዜጎች የሚገባዉን የክብር ሥፍራ እንዲሰጥ የምናስገድድበት ሁኔታ እንዘረጋለን።

ኢሕአዴግ በ 97 ም ቢሆን በሩን ሙሉ በሙሉ የከፈተበት ሁኔታ አልነበረም። ምርጫዉ እስኪደረግ አባላቶቻችን እየታሰሩ እየተገደሉና እየተሰደዱ ነዉ፤ በምርጫዉ ስንሳተፍ የነበረዉ። ያኔም ቢሆን ዉስን ስፍራ ተከፍቶ ያንን እድል በመጠቀም ስፍራዉን ለማስፋት በመቻላችን ነዉ ዉጤት ሊመጣ የቻለዉ። አሁን ገዢዉ ፓርቲ ያንን ጠባብ ስፍራ የመዝጋት አዝማሚያ አሳይቷል። ከዛም በኋላም ዜጎች ለመብቶቻቸዉ በሰላምዊ ትግል እምነት እንዲኖራቸዉ፣ ግንዛቢያቸዉ እንዲዳብር በዚህ ትግል ላይ ያላቸዉ እምነት እንዲጠነክር በማድረግ የትግሉን መሰረት እናሰፋለን። ድርጅታዊ ትሥሥራችንን በማጎልበት በአብዛኛዉ በራሳችን ላይ በመሥራትና አቅማችንን በማሳደግ በፊት ካገኘነዉ በላይ በሩን የማስከፈት እድል ይኖረናል ብዬ ነዉ የማምነዉ።

<u>አውደ</u>፦ ከመንግስት የሚጠብቃችሁ እንቅፋቶች ካለፈዉ እንዳየነዉ ከጥቃቅን ነገር ይጀምራል። ለዚህ ትዕግስት ኖሯችሁ ያሰባችሁትን ለዉጥ በአጭር ጊዜ ታሳካላችሁ ?

<u>ብርትኳን</u>፦ያለንበት ትግል የፖለቲካ ትግል ነዉ። ይሄ ደግሞ ትላንትም ዛሬም ወደፊትም ችግሮች እንደሚገጥሙት ይታወቃል። ትግል ያስባለዉም ይኸዉ ነዉ። ለየት የሚያደርገዉ የኛ ሀገር ትግል የሥልጣን ፉክክር ሳይሆን ስምምነት ላይ ያልተደረሰዉ የዲሞክራሲ መሰረቶች መጣሳቸዉ ላይ ነዉ። በ 97 ችግሮቹን በተወሰነ ደረጃ ባማለፋችን ሕዝቡ በሰላማዊ ትግል መንግስትን ለመቀየር የመቻሉን እምነት እንዲቀይር አድርገናል። አሁንም በመቀጠል ችግሮችን በማለፍ እንታገላለን።

ገዢዉ ፓርቲ ችግር መፍጠሩ የሚጠበቅም የተለመደም ነዉ። የአንድ ፖለቲካ ፓርቲ ብቃት የሚመዘነዉ ችግሮችን ሕዝቡስ አስተባብሮ ማለፍ በመቻሉ ላይ ነዉ። አንድ ሰላማዊ ትግልን ከሚመራ ፓርቲ የሚጠበቀዉን ከፈጸምን ችግሮችን ማለፍ የማንችልበት ምክንያት አይኖርም።

<u>አውደ</u>፦ የጋራ አመራር እንከተላለን እያላችሁ ነዉ። ከቀድሞ ቅንጅት የሚሻለዉ እና የሚለየዉ በምንድን ነው?

<u>ብርትኳን</u>፦ በመሰረቱ ቅንጅት ከመነሻዉ የነበረዉ ደንብ የአንድ ሰዉ አመራርን የማይከተል፣ የጋራ አሰራር ሥርዓትን ተጠያቂነትን የሥልጣን ክፍፍልን መርህ ያደረገ ነበር። የጋራ አመራር የሚለዉ በብዛት መደመጥ የጀመረዉ ችግሮች ጎልተዉ መዉጣት ሲጀምሩ ነዉ። በተለይ በሊቀመንበሩ አማክኝነት በራሳቸዉ ፍቃድና ፍላጎት ድርጅቱን ለመቀየር በሚሞክሩበት ጊዜ በደንባችን ለመጽናት ስንል ይህን ስንል ተደምጠን ይሆናል። ቅንጅት ከመነሻዉ እንደ ጥምረትም እንደ ዉህድ ፓርቲም ይህ ድንጋጌ በግልጽ አስቀምጦ ነበር። እኛም ስልጣን በብዙ ሃላፊዎች ዘንድ የተከፋፈለ አንደኛዉ ሃላፊ ለሌላዉ ተጠያቂነት እንዲኖረዉ በተለያየ ደረጃ የተቋቋመ ብዙ አባላት ያሉባቸዉ ብሄራዊ ምክርቤትና የሥራ አስፈጻሚ የምንላቸዉ ዉሳኔ የሚሰጡበት አቅጣጫ የሚያሲዙበት አካሄድን ነዉ የምንከተለዉ።

<u>አውደ</u>፦ የቅንጅት የሞራል ባለቤት ነን ትላላችሁ? ለምን ? ለስሙስ ለምን አልተከራከራችሁም ? ህዝቡም እናንተም መስዋዕት የሆናችሁት ለቅንጅት አይደለምን ?

<u>ብርትኳን</u>፦ ቅንጅት የሚለዉ ቃል ልዩ ትርጉም ያገኘዉ የኛ ፓርቲ መጠሪያ ከሆነ በኋላ ነበር። ቃሉ ዉስጥ አይደለም የፖለቲካ ተቀባይነት ያለዉ። ይዘን የተነሳነዉ አላማ፣ ራዕይና አመለካከት ነዉ። ቅንጅት የሚለዉ ቃል በሕብረተሰቡ ዘንድ ልዩ ስሜት የፈጠረዉ ለዚህ ነዉ። በርግጥ ለስሙ መከራከር ይቻል ነበር። እንደ አማራጭ በደንብ አይተነዋል። ለስሙ በመከራከር የሚወስደዉ ጊዜ፣ ሊገኝ የሚችለዉን ፍትህ ግንዛቤ ዉስጥ በማስገባት፣ የምርጫ ቦርድና ፍ/ቤት አሰራርን ከልምድ በማየት ስያሜዉ ለኛ የሚመጣበት ሁኔታ ዉስን መሆኑን በመረዳት፤ እዛ ክርክር ዉስጥ አልገባንም። ክርክር ዉስጥ ገብተን ብንቀጥል በየጊዜዉ አባላቶቻችን እስከአሁን በደረሱብን ችግርና ዉጣዉረድ የተበታተኑትን የባሰ እንዲበታተኑ ከማድረግ፣ ከፖለቲካ አመራሩ ጋር ግንኙነት የሚያደርጉበት መስመር እያጡ ድርጅታዊ አቅማችን እየተዳከም ከመሄድ ዉጭ የምናገኘዉ ጥቅም አልታየንም። ጽጌሬዳ በምንም ቢጠራ ጽጌረዳ ነዉ ብለን አባላቶቻችንንና ደጋፊዎቻችንን እንደገና ለማሰባሰብ በአዲስ ስያሜ ለመመዝገብ ወስነናል።

<u>አውደ</u>፦ ህዝቡ በቅንጅት መከፋፈል ግራ ተጋብቷል። በስሙና በሚከተለዉ መርህ እንሄዳለን እያሉ ለስሙ የሚከራከሩ ቡድኖች አሉ። እናንተም የቅንጅት መንፈስ የኛ ነዉ ትላላችሁ። ልዩነት ከሌለ አንድ ላይ መስራት ለምን አቃታችሁ ?

<u>ብርትኳን</u>፦ ቅንጅት ደጋግሞ እንደሚጠቀሰዉ በህገሪቱ ላይ ማየት ከሚፈልጋቸዉ እንዱና ዋናዉ በህገሪቱ የዲሞክራሲ ግንባታ ነዉ። ይህ ሕዝብ የፈለገዉን መርጦ ድምፁ በአግባቡ እንደሚቆጠርለት፣ የዜግነትና የእኩልነት መብቱ ተረጋግጦ ማየት ከአላማዎቹ ሁሉ ቅድሚያ የሚሰጠዉ ነዉ። በሂደት ግን የሚያጋጥሙንን ችግሮች ለመፍታት በሚሞክርበት ጊዜ እንደ ግለሰብም እንደ ስብስብም ለቆምንለት አላማ ምን ያህል ታማኝ ነን ብለን ተፈትነናል። ለዚህ ዓላማ የአንደበት አገልግሎት የሰጡት የዲሞክራሲ መብታቸዉን ተጠቅመዉ የራሳቸዉን መንገድ መርጠዋል።

የዓላማ ስምምነት አለ። የዓላማ ጽናት ላይ ግን ተለያይተናል። አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ብሎ ራሱን እንደገና ወደ ኢትዮጵያ ፖለቲካ ሥርዓት ዉስጥ ተደራጅቶ እየገባ ያለዉ ኃይል ለዛ ድርጅት ደንብ የበላይነትና ለዲሞራሲአዊ አሰራር፤ ለብዙሃን ዉሳኔ ታማኝነቱን ያረጋገጣ ኃይል ነዉ። የቅንጅትን አላማ የምር በመዉሰድና በቁርጠኝነት በመቆም ያረጋገጠ ስብስብ ይሄ ነዉ።

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ አርማና መዝሙር

በኢትዮጵያዊነት በአንድነት ድምፃችን
ለሰላም ለፍትህ በገባነው ኪዳን ...አዝማች
ለህዝባዊ ሥልጣን በፅናት ቆመናል
በአንድነት ጥላ ሥር ፓርቲ መሥርተናል።(2)

አለን ብዙ አደራ ዳር የሚደርስ ራዕይ (2)
የተጨበጠ ለውጥ ነግ ለህዝባችን በገሃድ የሚታይ
በወጣት በአዛውንት በወንድ በሴቱ በሁላችን ጥረት
በአንድነት ተጉዘን የምንደርስበት(2)።
አዝማች ...

ሰው በሰውነቱ በሀገሩ እንዲከበር (2የነፃነት መንፈስ
የዕኩልነት ብርሃን እንደበራ እንዲኖር
ለዲሞክራሲና ለሀገራዊ ዕርቅ ጸንተን እንሰራለን

በአንድነት ፓርቲያችን በጋራ እንቆማለን (2) ።
አዝማች ...

ለህዝባችን ተስፋ ለሀገር ፍቅር ስንል (2)
ትግላችን በቋንቋ በዖታ በሃይማኖት በዕድሜ ሳይነጠል
ምስራቅ ከምዕራብ ሰሜንን ከደቡብ በአንድ
ያስተሳስራል
የፓርቲያችን መርህ የጠራ ፕሮግራም ለሁሉም
ይሆናል።
አዝማች ...

# ቅንጅት በአንደበት...

ከገጽ 3 የዞረ

አውደ- አባላት ለማሰባሰብ ላይ ክልል ስትሄዱ ከመንግስት በተጨማሪ ይሄ ክፍፍል ችግር አልፈጠረባችሁም ?

ብርትኳን፦በመሃከላችን የነበረዉ ልዩነት የተወሰነ ተጽኖ ነበረዉ። ግን ከታች እስከ ገጠር ድረስ ያሉት አባላትንና ደጋፊዎች ስለሁኔታዉ ተገንዝበዉ ተገቢዉን ዳኝነት የመስጠት ብቃቶችን አሳይተዉናል። በቀድሞ ሊቀመንበራችን በኩል ያለዉ ስብስብ ይህን በመሃከላችን ያለዉን ልዩነት የተለየ መልክ አልብሶ ከስም ማጥፋት፣ ከሃሰተኛ ክስ ጋር አያይዞ ና ሌላዉን የፖለቲካ ሥራ ትቶ እንዲህ አይነት ዘመቻ ሲያካሄድብን ነበር። የተለያዩ ሲዲዎችን ፣ መረጃዎችን በጣም በተዛባ መልኩ እንዲኖራቸዉ እየቀረጡና እየቀጠሉ በየቦታዉ አሰራጭተዉ ነበር። እኛም በተወሰነ ደረጃ አባላቶቻችንን ለማግኘትና ሂደቱን ለማስረዳት ስንሞክር የግለሰብን ስም እየጠሩ እንዲህ ነዉ ከማለት፣ ከእነርሱ የለየን የመርህ ጉዳይ መሆኑን፣ መርሁም ዜጎች የሞቱለት በመሆኑ ከዚህ አላማ ዙሪያ ከወጣን የድርጅቱን የምንነት መለያዉን እንዲያጣ በማስረዳት አብዛኛዉን አባላት የሚጠብቁት በአፋጣኝ ቢሮዎች ተከፍተዉ መደበኛ የፖለቲካ ስራ የምንሰራበትን ወቅት መሆኑን ተግባብተናል።

አውደ፦ ቢሮ ለመክፈትና ሕጋዊ ሰርተፊኬት ለማግኘት ስትንቀሳቀሱ ገዢዉ ፓርቲ ችግር ሊፈጥርባችሁ እንደሚችል ገምታችሁ ነበር ?

ብርትኳን፦ ጠቅላላ ጉባዔ መካሄዳ ላይ የገጠምን ችግር ገዢዉ ፓርቲ ምን ሊያደርግ እንደሚችል በጥሩ ሁኔታ አስተምሮናል። ሰላማዊ ትግል እንዲሁ ነዉ፤ ችግር ይገጥመዋል። ችግሩ እኛን ለማስቆም ነዉ። “በቃ አይሆንም; መንገዱ ሁሉ ዝግ ነዉ” ብለን እንድንቀመጥና ተስፋ እንድንቆርጥ ነዉ የሚፈለገዉ። ከኛ የሚጠበቀዉ የሚገጥመንን ችግር የሚያቆም ሳይሆን ማለፊያ መንገዱን ፈልገን በጽናት ወደፊት የምንሄድበትን ሁኔታ መፍጠር እንዳለብን ነዉ። በተለይ ከርምጫ ቦርድ የተለያዩ አደናቃፊ ሁኔታዎች ሊገጥሙ ይችላሉ። በተቻለን መጠን እነዚህን መሰናክሎች የምናልፍበት ስልት ቀይሰን እንቀጥላለን ብለን ነዉ የምናምነዉ።

አውደ፦ ነጻዉ ፕሬስ ፣ የብሄራዊ ባንክ ማሻሻያ፣ የፖለቲካን ፓርቲ በሚመለከት፤ ሕጎች እየተረቀቁ ነዉ። ኢሕአዴግ ወደ ማዕከላዊነት እየተመለሰ ህገሪቷ የበለጠ ችግር ዉስጥ እየገባች ባለበት ሰዓት የናንተ ፓርቲ መመስረት ለሕዝብ ተስፋ ነዉ እየተባለ ነዉ። በርግጥ ተስፋ ሆናችሁ ቁልቁል የሚኳዘዉን ዲሞክራሲ ትመልሳላችሁ ? እናንተስ ላይ ተጽኖ አያሳድርም ?

ብርትኳን፦የፖለቲካ ስፍራዉን የሚያጠቡ ድንጋጌዎች በየጊዜዉ እየተረቀቁ መሄዳቸዉ አሳሳቢ ነዉ። እነዚህ ሁኔታዎች ስላሉ የሚኖረዉ አማራጭ ምንድን ነዉ የሚለዉን እናያለን። ጥሩ ምሳሌ የሚሆንን የ 97 ምርጫ ነዉ። ያኔ ኢሕአዴግ የፖለትካ ስፍራዉን ሲከፍተዉ ለዲሞክራሲ ግንባታ፣ ለመድበለ ፓርቲ ስርዓት መመስረት ባህሪዉን ለዉጦ ነበር ወይ ? ስልጣኔንንም ቢሆን አጥቼ ይህን ነገር በኢትዮጵያ ዳብሮ ማየት እፈልጋለሁ ብሎ ነበር ወይ ? የሚለዉን ስናይ ከምርጫዉ በኋላ የተወሰዱ እርምጃዎች ከልብ የሆነ ሚስጥራዊ የለዉጥ ፍላጎት እንዳልነበረዉ ግልጽ አድርጎልናል። የእምነት ለዉጥ ካልነበረ ሌሎች ምክንያቶች ናቸዉ ወደዚያ የመሩት ማለት ነዉ። የሃገራችን ኢኮኖሚ የተመሰረተዉ በዉጭ እርዳታ በመሆኑ እነዚህ አካላት ግፊት አድርገዉበት ነበር ማለት ይቻላል። በሕዝቡ ዘንድ የነበረዉ የለዉጥ ስሜት ተጨማሪ ሆኖ ለዛ ሁኔታ የተገፋ ይመስላል። አሁንም እነዚህ ግፊቶችና ተጽኖዎች በዲፕሎማቲክ ማህበረሰቡ እና በህዝቡ መሃከል በማኖር አቅጣጫ ግፊት እንዲደረግበት በማድረግ ይህን ወደ መዝጋት እየሄደ ያለዉን ሳይወድ በግድ ከፍቶ እንዲሄድ የምናደርግበት ሁኔታን መፍጠር የኛ ድርሻ ነዉ። በጣም ከባድ ነዉ። ግን በአግባቡ ከታሰበበትና እስከአሁን በተቃዉሞ ፖለቲካ ዉስጥ ያልታዩና ያልተጠቀምንባቸዉን ክፍተቶች ከተጠናና ወደ ተግባር እስክገባን ድረስ (ምናልባት ረዘም ያለ ጊዜ ሊወስድ ቢችልም) እንዲህ አይነት ጫና በመንግስት ላይ መፍጠር የማንችልበት ሁኔታ የለም ብዬ አምናለሁ።

ፓርቲዊ ለዉጥ ማድረግ ካለበት፤ ኢሕአዴግ ምን አደረገ ወይም ሊያደርግ ይችላል? ምን አይነት አሉታዊ ተግባራትን በፖለቲካ ሂደት ሊፈጽም ይችላል? ከሚለዉ ይልቅ እኛ ያንን ለመለወጥ ምን ማድረግ እንችላለን፤ የህብረትሰቡን አመለካከት ለመለወጥ ባለዉ ዉስን ስፍራ አባላቶችን እንዴት ማሰባሰብ እንችላለን? የተሰበሰቡት አባላት እንዲሁ በደመ ነፍስ የሚከተሉን ሳይሆን ልዩነታችን በትክክል የገባቸዉ ሆኖ ለዲሞክራሲ አመለካከቶች ታማኝነታቸዉ የተረጋገጠ፤ ራሳቸዉን የለወጡ ድርጅታቸዉንም በዛዉ የፖለቲካ አመለካከታቸዉ ሊያንጹት ቁርጠኝነት ያላቸዉ አባላትን በማፍራት ላይ ማተኮር ነዉ ያለብን። ለዲሞክራሲ ግንባታ ለፖለቲካ ስርዓት ሂደቱ ገዢዉ ፓርቲ ያለዉ ሚና የሚናቅ እንዳልሆነ ይታወቃል። ነገር ግን ተጨዋቹ እርሱ ብቻ አይደለም። እኛም ተጨዋቾች ነን። የመጨወቻዉ ሜዳዉ መጥበብ እኛ ላይ ተጽኖ መፍጠሩ አይቀርም። ቢሆንም ልናደርገዉ የምንችለዉ በእጃችን ፤ በራሳችን ብቃት ያለ ነዉ። ከምንም በላይ ደግም የተባበረና የተደራጀ ጉልበት መባከን የለበትም። ህዝቡ በራሱ ላይ ያለዉን እምነት እንዲገነባ ለለዉጥ ያለዉ ፍላጎት እንዲነቃቃ እና የሚገጥመዉን ችግር ጽናትን የሚፈጥር እንጂ ተስፋ መቁረጥን የሚያመጣ እንዳይሆን ተጠንቅቆ ድርጅቱ በታለመዉ አቅጣጫ ትግሉን እንድንቀጥል የማበረታታት፣ የማደራጀት ሃላፊነት ከኛ ይጠበቃል። ፍርሃትን በድፍረት ተስፋ መቁረጥን በጽናት ለማስለወጥ መስራት ከአመራሩ ይጠበቃል። አመራር በማጣቱ የመደብዘዝ. የመንፈስ መዳከም ሊኖር ቢችልም፤ አስፈላጊዉን አመራር እስካገኘ ድረስ በቀላሉ እደገና ፍርሃትን ለዉጠ ለሙብቱ ለመታገል እንደሚችል እርግጠኛ ነኝ።

# ሰበር ዜና

## “መድረክ ለዲሞክራሲያዊ ምክክር በኢትዮጵያ”

ኢትዮጵያ ውስጥ ዲሞክራሲን ለማስፈን በሀገር ውስጥ በሰላማዊ ትግል እየተንቀሳቀሱ ያሉ አራት ድርጅቶችና ሁለት በግል የሚንቀሳቀሱ “መድረክ ለዲሞክራሲያዊ ምክክር በኢትዮጵያ” የሚል የጋራ መድረክ ማቋቋማቸው ተገለጸ። እነሱም፦

የኦሮሞ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኦፌዲን)

የሶማልያ ዲሞክራሲያዊ ሃይሎች ቅንጅት

አረና ትግራይ ለዲሞክራሲና ሉአላዊነት (አረና)

የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሃይሎች ህብረት (ህብረት)

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ - የቀድሞ ፕሬዝዳንትና በግል የፓርላማ ዓባልና አቶ ስዬ አብረሀ ናቸው።

በዚህ መድረክ ምስረታ ላይ፤ አንድነት ፓርቲ በታዛቢነት ደረጃ መሳተፉ ታውቋል። ፓርቲውን ወክለው በመድረክ ምሥረታ ላይ የተገኙት ዶ/ር ያቆብ ሃ/ማርያም ናቸው። የመድረክ ዋነኛ እሴቶች፤ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን መገንባት፤ የሀገር አንድነትና ሉዓላዊነትን ማስከበርና ህዝባዊ ሰላማዊ የትግል ስልትን መከተል፤ መሆናቸው ታውቋል።

አትላንታ * ቦስተን * ችካጎ * ዳላስ * ዴነቨር * ሎሳንጀለስ* ላስሽገስ * ሚኒያፖስ * ናሽቪል *
ኦክላነድ * ኦሃዮ * ፊኒክስ * ሳንሆዜ * ሲያትልን * ደቡብ ዳኮታ *አፕ ስቴኢት*ኒኦርክ*ዋሽንግትን ሜትሮ

የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ በሰሜን አሜሪካ ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች ማኅበር

766 Rock Creek Church Rd., NW .Washington DC, 20010 *ስልክ (202) 541-0556
ፋክስ: (202) 541-0557.*ኢሜል: kinijitna@kinijitna.org
Www.kinijitna.org

አስተያየቶን በ awdeethiopia@gmail.com ይጻፉልን